# ታቦትና አዲስ ኪዳን

1 የታቦት አመጣጥና ምንነት ........ 1
1.1 ብሉይ ኪዳን (የቀድሞው ኪዳን) ........ 1
1.2 የቃል ኪዳኑ ተጋቢዎች ........ 2
1.3 የቃል ኪዳኑ ይዘት ........ 3
1.4 የታቦት ምንነት ........ 4
2 የብሉይና የአዲስ ኪዳን ልዩነት ........ 5
3 ታቦት በዮሐንስ ራእይ ........ 8

## 1 የታቦት አመጣጥና ምንነት

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነው ከአንዳንድ ወገኖች የሚደርሰን ጥያቄ ነው። ጥያቄውም ታቦትን የተመለከተ ሲሆን፤ በተለይ በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ላይ ታቦት መጠቀሱ አንዳንዶች ላይ ጥያቄ መፍጠሩ አልቀረም። ታቦት በዮሐንስ ራእይ ከተጠቀሰ ታዲያ በአዲስ ኪዳንም ያስፈልጋል ማለት ነው? በዮሐንስ ራእይ ላይ መጠቀሱስ ምን ያስተምረናል ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ። ከዚህ በመቀጠል በታቦትና በአዲስ ኪዳን ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎችን በአጭሩ ለመመልስ እንሞክራለን።

በአዲስ ኪዳን ታቦት ያስፈልጋል ወይም አይስፈልግም የሚለውን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ስለ ታቦት ምንነት ትንሽ እንመልከት።

የታቦትን ወይም መጽሐፍ ቅዱስ በአብዛኛው እንደሚጠራው "የኪዳን ታቦት" ወይም "የምስክር ታቦት"ን ምንነት በሚገባ ለመረዳት ደግሞ ታቦቱ የተሰጠበትን የብሉዩን ቃል ኪዳን መረዳት ያስፈልጋል። ታቦት ወይም "የቃል ኪዳን ታቦት" እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በሙሴ በኩል የገባው የቃል ኪዳኑ ምልክትና ምስክር ነው። ስለዚህ የኪዳኑን ታቦት ምንነት ለመረዳት ኪዳኑን ወይም ቃል ኪዳኑን ራሱን መረዳት ያስፈልጋል።

### *1.1 ብሉይ ኪዳን (የቀድሞው ኪዳን)*

እግዚአብሔር የቃል ኪዳን አምላክ ነው። በተለያዩ ጊዜያት እግዚአብሔር ከግለሰቦችና ከእስራኤል ሕዝብም ጋር ቃል ኪዳን ገብቶአል። ከግለሰቦች ጋር ከገባቸው ቃል ኪዳኖች ውስጥ ከኖህ፤ ከአብርሃምና ከዳዊት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ደግሞ ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት ነጻ ካወጣቸው በኋላ በምድረበዳ በሲና ተራራ የገባው ቃል ኪዳን ማለትም ብሉይ ኪዳን ወይም የቀድሞው ኪዳን የሚጠቀስ ነው።

ቃል ኪዳን ማለት በሁለት ሰዎች ወይም በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የሚገባ የስምምነት ውል ነው። ስለዚህ የብሉዩንም ይሁን የአዲሱን ቃል ኪዳን ለመረዳት የስምምነቱ ውል ይዘት ምን እንደሆነና ቃል ኪዳን ተጋቢዎቹስ እነማን እንደሆኑ ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል። ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ግልጽ ከሆነልን በብሉይና በአዲስ ኪዳን ልዩነት ዙሪያ የምንጠይቃቸው ብዙ ጥያቄዎቻችን ይመለሱልናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘጸዐት ከምዕራፍ 19-24 ላይ ስናነብ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር እንዴት ብሉይ ኪዳንን እንደሰጣቸው ወይም ከእነርሱ ጋር እንዴት ቃል ኪዳን እንዳደረገ እንመለከታለን።

በመጀመሪያ በምዕራፍ 19 ላይ እግዚአብሔር ራሱ በሲና ተራራ ላይ እንደወረደና በቀጥታ እንደተናገራቸው እናያለን።

> ኦሪት ዘጸአት 19
> 1 በሦስተኛውም ወር የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር ከወጡ በኋላ በዚያ ቀን ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ። 2 ከራፊድም
> ተነሥተው ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ፥ በምድረ በዳም ሰፈሩ በዚያም እስራኤል በተራራው ፊት ሰፈረ። 3 ሙሴም ወደ
> እግዚአብሔር ዘንድ ወጣ እግዚአብሔርም በተራራው ጠርቶ አለው። **ለያዕቆብ ቤት እንዲህ በል፥ ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ
> ንገር**። 4 በግብፃውያን ያደረግሁትን፥ በንስርም ክንፍ እንደተሸከምኋችሁ፥ ወደ እኔም እንዳመጣኋችሁ አይታችኋል። 5 አሁንም
> ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ 6
> እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ። **ለእስራኤል ልጆች** የምትነግራቸው ቃል ይህ ነው።

> ኦሪት ዘጸአት 19
> 16 እንዲህም ሆነ በሦስተኛው ቀን በማለዳ ጊዜ **ነጐድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና እጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምጽ**
> በተራራው ላይ ሆነ በሰፈሩም የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ተንቀጠቀጡ። 17 ሙሴም ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘት ከሰፈር
> አወጣቸው ከተራራውም እግርጌ ቆሙ። 18 **እግዚአብሔርም በእሳት ስለ ወረደበት የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር** ከእርሱም እንደ
> እቶን ጢስ ያለ ጢስ ይወጣ ነበር፥ **ተራራውም ሁሉ እጅግ ይናወጥ ነበር**። 19 የቀንደ መለከቱም ድምፅ እጅግ በበረታና በጸና ጊዜ

*ሙሴ ተናገረ እግዚአብሔርም በድምፅ መለሰለት።*

እግዚአብሔር እንደዚህ በነጎድጓድና በመብረቅ ድምጽ በምድርም መናወጥ በሲና ተራራ ለእስራኤል ሕዝብ ከተገለጠ በኋላ በምዕራፍ 20 አሥርቱን ትዕዛዛት ለሕዝቡ ይሰጣቸዋል። እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የገባው ይህ ቃል ኪዳን ወይም ብሉይ(የቀድሞ) ኪዳን ያካተተው አሥርቱን ትዕዛዛት ብቻ አይደለም። አሥርቱን ትዕዛዛት ጨምሮ ከምዕራፍ 20 እስከ ምዕራፍ 23 ያሉትን የተለያዩ ሕጎችን ሁሉ ያካተተ ነው። ከምዕራፍ 20 እስከ ምዕራፍ 23 ብዙ ሕግጋትን ሕዝቡ እንዲጠብቁ እግዚአብሔር ከነገራቸው በኋላ ሕዝብም እነዚህን ሕግጋት እንደሚጠብቁ ቃል ገብተው ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ያደርጋሉ።

> ኦሪት ዘጸአት 24
> 3 *ሙሴም መጣ ለሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃሎች ሁሉ ሥርዓቱንም ሁሉ ነገረ ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ድምፅ።* ***እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎች ሁሉ እናደርጋለን ብለው መለሱ።*** 4 *ሙሴም የእግዚአብሔርን ቃሎች ጻፈ ማለዳም ተነሣ፥ ከተራራውም በታች መሠዊያን፥ አሥራ ሁለትም ሐውልቶች ለአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ሠራ።* 5 *የሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርቡ፥ ለእግዚአብሔርም ስለ ደኅንነት መሥዋዕት በሬዎችን እንዲሠዉ የእስራኤልን ልጆች ጕበዛዝት ሰደደ።* 6 *ሙሴም የደሙን እኵሌታ ወስዶ በቆሬ ውስጥ አደረገው የደሙንም እኵሌታ በመሠዊያው ረጨው።* 7 *የቃል ኪዳኑንም መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ አነበበላቸው እርሱም፦ እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም አሉ።* 8 ***ሙሴም ደሙን ውስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው። በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ አለ።***

በዚህ ክፍል እንግዲህ እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር "ብሉይ ኪዳን" ወይም የቀድሞው ኪዳን ተብሎ የሚጠራውን ቃል ኪዳን ሲገባ እንመለከታለን።

## *1.2 የቃል ኪዳኑ ተጋቢዎች*

በመጀመሪያ በዚህ በዘጽአት እንዲሁም በብሉይ ኪዳን ባጠቃላይ የምንመለከተው የብሉዩ ቃል ኪዳኑ የተፈጸመው በእግዚአብሔርና በእስራእል ሕዝብ መካከል ነው።

> ኦሪት ዘጸአት 19፤3
> ***… ለያዕቆብ ቤት እንዲህ በል፥ ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ንገር***

ይህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ከግብጻዊያን ወይም ከኢትዮጵያውያን ወይም ከሌሎች ሕዝቦች ጋር የገባው ቃል ኪዳን አይደለም። ይህ እግዚአብሔር ፊት ለፊት ተገልጦ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የገባው ኪዳን ነው። ተሰድደው ወደ እስራኤል አገር ምጻተኛ (ስደተኛ) ሆነው ከሚኖሩ በስተቀር ማናቸውንም እስራኤላዊ ያልሆኑ ሕዝቦችን ያካተተ አይደለም። እንዲያውም እስራኤላውያን ከሌሎች ሕዝቦች ተለይተው ለእግዚአብሔር እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው።

> ኦሪት ዘጸአት 19፤5
> *አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና* ***ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ***

ቃል ኪዳኑን ከእግዚአብሔር ጋር ያሰሩት ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ በቀጥታ የተወለዱ እስራኤላውያን ናቸው። እናደርጋለን ብለውም ቃል የገቡት እነርሱ ናቸው። ቃል ኪዳኑ የታሰረበትንም ደም የተረጩት እነርሱው ናቸው። የቃል ኪዳኑም መታሰቢያ ሐውሎቶች የተሠሩት ለአሥራ ሁለቱ የእስራእል ነገዶች ነው።

> ኦሪት ዘጸአት 24
> 3 *ሙሴም መጣ ለሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃሎች ሁሉ ሥርዓቱንም ሁሉ ነገረ ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ድምፅ።* ***እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎች ሁሉ እናደርጋለን ብለው መለሱ።*** 4 *ሙሴም የእግዚአብሔርን ቃሎች ጻፈ ማለዳም ተነሣ፥ ከተራራውም በታች መሠዊያን፥* ***አሥራ ሁለትም ሐውልቶች ለአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ሠራ።*** 5 *የሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርቡ፥ ለእግዚአብሔርም ስለ ደኅንነት መሥዋዕት በሬዎችን እንዲሠዉ የእስራኤልን ልጆች ጕበዛዝት ሰደደ።* 6 *ሙሴም የደሙን እኵሌታ ወስዶ በቆሬ ውስጥ አደረገው የደሙንም እኵሌታ በመሠዊያው ረጨው።* 7 *የቃል ኪዳኑንም መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ አነበበላቸው እርሱም፦* ***እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም አሉ።*** 8 ***ሙሴም ደሙን ውስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው። በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ አለ።***

ይህ የብሉዩ ኪዳን አሕዛብን ማለትም እስራኤላዊ ያልሆኑትን እንደ ግብጽ፤ ኢትዮጵያ ወዘተ የመሳሰሉትን ሕዝቦች የማያካትት ወይም የማያቅፍ ኪዳን ነው። እንዲያውም እስራኤላውያን ከአሕዛብ ጋር እንዳይጋቡ የሚከለክል አሕዛብን ከኪዳኑ የሚያገልል (exclude) የሚያደርግ ኪዳን ነው።

> ኦሪት ዘዳግም
> 7፥3 ከእነርሱም ጋር አትጋባ ሴት ልጅህን ለወንድ ልጁ አትስጥ፥ ሴት ልጁንም ለወንድ ልጅህ አትውሰድ።

ከዚህ በተጨማሪ ኪዳኑ ከአንድ ሕዝብ ብቻም ሳይሆን ከአንድ አገር ጋርም የቆራኘ ነው። ከእስራኤልን ሕዝብና እግዚአብሔር ለእነ አብርሃም ከሰጣቸው ከእስራኤል ምድር (ከነዓን) ጋር የተቆራኘ ኪዳን ነው።

ኦሪት ዘዳግም 4
37-38 **አባቶችህን ወድዶአልና ከእነርሱ በኋላ ዘራቸውን መረጠ**፥ ዛሬ እንደ ሆነው ሁሉ ከአንተ የጸኑትን ታላላቆችን አሕዛብ
በፊትህ እንዲያወጣ፥ አንተንም እንዲያገባህ፥ ምድራቸውንም ርስት አድርጎ እንዲሰጥህ፥ ከአንተ ጋር ሆኖ በታላቅ ኃይሉ ከግብፅ
አወጣህ። 39 እንግዲህ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም በምድር አምላክ እንደ ሆነ፥ ሌላም እንደሌለ ዛሬ እወቅ፥ በልብህም
ያዝ። 40 **ለአንተ ከአንተም በኋላ ለልጆችህ መልካም ይሆን ዘንድ፥ አምላክህም እግዚአብሔር ለዘላለም በሚሰጥህ ምድር**
**ዕድሜህ ይረዝም ዘንድ፥ እኔ ዛሬ የማዝዝህን ሥርዓቱንና ትእዛዙን ጠብቅ።**

ኦሪት ዘዳግም 4
1 አሁንም፥ **እስራኤል ሆይ**፥ እንድታደርጉአቸው በሕይወትም እንድትኖሩ፥ የአባቶቻችሁም አምላክ እግዚአብሔር **ወደሚሰጣችሁ**
**ምድር ገብታችሁ እንድትወርሱ**፥ የማስተምራችሁን ሥርዓትና ፍርድ ስሙ።

25 ልጆችን የልጅ ልጆችንም፥ በወለዳችሁ ጊዜ በምድሪቱም ብዙ ዘመን በተቀመጣችሁ ጊዜ፥ በረከሳችሁም ጊዜ፥ በማናቸውም
ቅርጽ የተቀረጸውን ምስል ባደረጋችሁ ጊዜ፥ ታስቈጡትም ዘንድ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር በሠራችሁ
ጊዜ፥ 26 ትወርሱአት ዘንድ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ **ከምትገቡባት ምድር ፈጥናችሁ እንድትጠፉ** እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን
በእናንተ አስመሰክራለሁ ፈጽሞም ትጠፋላችሁ እንጂ ረጅም ዘመን አትቀመጡባትም። 27 እግዚአብሔርም **በአሕዛብ መካከል**
**ይበትናችኋል**፥ እግዚአብሔር በውስጣቸው በሚያኖራችሁ በአሕዛብ መካከልም ጥቂቶች ሆናችሁ ትቀራላችሁ።

ማንን ነው በነዚህ ክፍሎች "እስራኤል ሆይ" እያለ እግዚአብሔር የሚናገረው? የሰጣቸውን የብሉዩን ኪዳን ትዕዛዝ ቢጠብቁ በሚሰጣቸው ምድር እንደሚባርካቸው የሚናገረው እነማንን ነው? ትዕዛዛቱን ባይጠብቁ ደግሞ ከሰጣቸው ምድር አውጥቶ እንደሚበትናቸው የሚናገረው እነማንን ነው? መልሱ የእስራኤልን ሕዝብ ነው የሚል ነው። ለሌላ ሕዝብማ እንደዚህ ያለ አገርና ከአገሩ ጋር የተቆራኘ ኪዳን አልተሰጣቸውም።

እነዚህ ክፍሎች ግልጽ እንደሚያደርጉልን የብሉይ ኪዳኑ ውል በሥጋ ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ ከሚወለዱት ከእስራኤል ሕዝብና እግዚአብሔርም ከግብጽ ባርነት አውጥቶ ከሚሰጣቸው ምድር ጋር የተቆራኘ ኪዳን ነው። የኪዳኑ በረከትም መርገሙም ከእስራኤል ሕዝብና እግዚአብሔር ከሰጣቸው ከከነዓን ምድር ጋር የተሳሰረ ነው። ይህ ኪዳን ግሪካውያንን ወይም ግብጻዊያንን ወይም ኢትዮጵያውንን የሚመለከት ኪዳን አይደለም። እንዲያውም የሚያገልል እንጂ። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን የተካተተው የከነዓንን ምድር የመውረስ ጉዳይ ቢሆን ወይም በከነዓን ምድር መባረክ የአንድ ሕዝብና የአንድ አገር ኪዳን ብቻ እንደሆነ መገንዘብ ከብዙ ግራ መጋባቶች ይጠበቀናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ ይኖሩ ለነበሩና በሥጋ እስራኤላዊ ላልሆኑ ለአዲሱ ኪዳን አማኞች በቀድሞው ኪዳን ምንም ቦታ እንዳልነበራቸው ሲናገር እንዲህ ይላል፦

ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2
11 ስለዚህ እናንተ አስቀድሞ በሥጋ አሕዛብ የነበራችሁ፥ በሥጋ በእጅ የተገረዙ በተባሉት ያልተገረዙ የተባላችሁ፥ ይህን አስቡ፤ 12
በዚያ ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ
ከእግዚአብሔርም ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ።

## *1.3 የቃል ኪዳኑ ይዘት*

ማናቸውም ቃል ኪዳን የተመሠረተበት ውል ወይም ስምምነት አለው። ይህም ሁለቱ ቃል ኪዳን ተጋቢዎች ሊፈጽሙትና ሊጠብቁት ያለ ኃላፊነትን ሁለቱም በሚገባቸው ቋንቋ የሚገልጽ ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የገባው ይሄ ቃል ኪዳን ዋናው ውል ሕዝቡ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሕግጋት እንደሚጠብቁና ሕዝቡ ይሄን ካደረጉ ደግሞ እግዚአብሔር በበኩሉ አምላክ እንደሚሆናቸውና በሚሰጣቸው ምድር እንደሚባርካቸው የሚገልጽ ነው።

ኦሪት ዘጸአት 19
5 አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት
ትሆኑልኛላችሁ እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ።

ኦሪት ዘዳግም 4
40 ለአንተ ከአንተም በኋላ ለልጆችህ መልካም ይሆን ዘንድ፥ አምላክህም እግዚአብሔር ለዘላለም በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ
ይረዝም ዘንድ፥ እኔ ዛሬ የማዝዝህን ሥርዓቱንና ትእዛዙን ጠብቅ።

እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባው ይህ ቃል ኪዳን በረከት ብቻ ሳይሆን መርገምም ያዘለ ነው። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን

ሕግጋት ቢጠብቅ በረከትን እንደሚባረክና እንዲሁ ደግሞ ሕግጋቱን ባይጠብቅ እንደሚረገም የሚገልጽ ቃል ኪዳን ነው።

ኦሪት ዘዳግም 11
26 እነሆ፥ እኔ ዛሬ በፊታችሁ በረከትንና መርገምን አኖራለሁ 27 በረከትም፥ እኔ ዛሬ ለእናንተ የማዝዘውን የአምላካችሁን
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ብትሰሙ 28 መርገምም፥ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባትሰሙ፥ ዛሬም ካዘዝኋችሁ መንገድ
ፈቀቅ ብትሉ፥ ሌሎችንም የማታውቋቸውን አማልክት ብትከተሉ ነው።

ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 28 ላይ በቃል ኪዳኑ ውስጥ የተካተተው በረከትና መርገም በዝርዝር ተቀምጦአል።

እንግዲህ የዚህ የብሉይ ኪዳን መሠረት ወይም የቃል ኪዳኑ ውል ዋና ይዘት እግዚአብሔር የሰጠው ሕግጋት ናቸው። በረከቱም መርገሙም እነዚህን ሕግጋት በመጠበቅ ወይም ባለመጠበቅ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

## *1.4 የታቦት ምንነት*

ኦሪት ዘጸአት 25
1 እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው። 2 ስጦታ ያመጡልኝ ዘንድ **ለእስራኤል ልጆች** ተናገር...
8 **በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ**። 9 እኔ እንደማሳይህ ሁሉ፥ እንደ ማደሪያው ምሳሌ እንደ ዕቃውም ሁሉ
ምሳሌ፥ እንዲሁ ሥሩት። 10 **ከግራር እንጨትም ታቦትን ይሥሩ** ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፥
ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን። 11 በውስጥና በውጭም በጥሩ ወርቅ ለብጠው በእርሱም ላይ በዙሪያው የወርቅ አክሊል
አድርግለት። 12 አራት የወርቅ ቀለበቶችም አድርግለት፥ እነርሱንም በአራቱ እግሮቹ ላይ አኑር በአንድ ወገን ሁለት ቀለበቶች፥
በሌላው ወገን ሁለት ቀለበቶች ይሁኑ። 13 መሎጊያዎችንም ከግራር እንጨት ሥራ፥ በወርቅም ለብጣቸው። 14 ለታቦቱ
መሸከሚያ በታቦቱ ጐን ባሉት ቀለበቶች መሎጊያዎቹን አግባ። 15 መሎጊያዎቹም በታቦቱ ቀለበቶች ውስጥ ይኑሩ፥ ከቶም
አይውጡ። 16 **በታቦቱም ውስጥ እኔ የምሰጥህን ምስክር ታስቀምጣለህ።**

ቀድም ብለን እንዳየነው በዘጸአት 24 ላይ እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን ከገባ በኋላ በዚህ በዘጸአት 25 ላይ ደግሞ እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ መካከል እንዲኖር ቤተመቅደስን እንዲሠሩለት ሲያዝ እንመለከታለን። ከቤተመቅደሱ ጋር አያይዞ ታቦትን ከግራር እንጨት እንዲሠሩና በታቦቱ ውስጥም እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን "ምስክር" እንዲያስቀምጡ ሲያዛቸው እንመለከታለን። የታቦቱ እንግዲህ ዋናው ዓላማ በዚህ ክፍል "ምስክር" ተብሎ የተጠራውን ነገር ማስቀመጫ እንዲሆን ነው። ስለዚህ ታቦቱ ይህ "ምስክር" ተብሎ ከተጠራው ነገር ጋር የተቆራኘ ነው ማለት ነው።

ኦሪት ዘጸአት 31
18 እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ **በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን <u>የምስክር</u> ጽላቶች** ሰጠው።

ኦሪት ዘዳግም 4
3 ታደርጉትም ዘንድ ያዘዛችሁን ቃል ኪዳን **አሥሩን ቃላት** ነገራችሁ **በሁለቱም በድንጋይ ጽላቶች** ላይ ጻፋቸው።

ኦሪት ዘዳግም 10
4 ስብሰባ ተደርጎ በነበረበትም ቀን እግዚአብሔር በተራራው ላይ በእሳት ውስጥ ሆኖ የተናገራችሁን **አሥርቱን ቃላት ቀድሞ ተጽፈው እንደ ነበረ በጽላቶቹ ላይ ጻፈ እግዚአብሔርም እነርሱን ለእኔ ሰጠኝ።** 5 ተመልሼም ከተራራው ወረድሁ፥ **<u>ጽላቶችንም በሠራሁት ታቦት ውስጥ አደረግኋቸው</u>** እግዚአብሔርም እንዳዘዘኝ በዚያ ኖሩ።

እነዚህ ክፍሎች ደግሞ በታቦቱ ውስጥ የሚቀመጡትን "ምስክር" ተብለው የተጠሩትን ነገሮች ምንነት ግልጽ ያደርጉልናል። በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው "ምስክር" ተብለው የተጠሩት አሥርቱ ቃላት "በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸው" ድንጋዮች ወይም ጽላቶች ናቸው። እነዚህ እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች በታቦቱ ውስጥ እንዲያኖሩት የሰጣቸው አሥርቱ ቃላት የተጻፈባቸው ሁለቱ የድንጋይ ጽላቶች እግዚአብሔርና የእስራኤል ሕዝብ በሲና ተራራ ቃል ኪዳን እንደተጋቡ የሚመሰክሩ ምስክሮች ናቸው።

ቀደም ብለን እንዳየነውም የዚህ ቃል ኪዳን የውል ስምምነት መካከለኛና የኪዳኑ በረከትም ይሁን መርገም መሠረት እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የሰጠው ሕግ ስለሆነ እነዚህ አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፉባቸው ሁለት የድንጋይ ጽላቶች የብሉይ ኪዳኑ መሠረት ሕጉ እንደሆነና የእስራኤልም ሕዝብ በሙሉ አፍ እንደሚፈጽሙዋቸው ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን መግባታቸውን የሚያመለክቱ የብሉዩ ኪዳን ምስክሮች ናቸው።

ስለዚህ ታቦቱና በውስጡ የተቀመጡት የድንጋይ ጽላቶች የብሉዩ ወይም የቀድሞው ቃል ኪዳን ምስክሮች ስለሆኑ ከብሉዩ ኪዳን ጋር የተቆራኙና ተነጣጥለው ሊታዩም የማይችሉ ናቸው። ለዚህ ነው ታቦቱ ራሱ "የኪዳን ታቦት" ወይም "የምስክር ታቦት" እየተባለ የሚጠራው። ለብሉዩ ኪዳን መሠረትና ምስክር የሆኑትን ሕግጋት ስለያዘና ከብሉዩ ኪዳን ጋር የተቆራኘ ስለሆነ።

ኦሪት ዘጸአት
26፥33 መጋረጃውንም ከመያዣዎቹ በታች ታንጠለጥለዋለህ፥ በመጋረጃውም ውስጥ **የምስክርን ታቦት** አግባው መጋረጃውም
በቅድስቱና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል መለያ ይሁናችሁ።

ኦሪት ዘጸአት
40፥3 በእርሱም ውስጥ **የምስክሩን ታቦት** ታኖራለህ፥ ታቦቱንም በመጋረጃ ትጋርዳለህ።

ኦሪት ዘዳግም
10፥8 በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔርን **ቃል ኪዳን ታቦት** ይሸከም ዘንድ፥ እርሱንም ለማገልገል በእግዚአብሔር ፊት ይቆም ዘንድ፥
በስሙም ይባርክ ዘንድ እግዚአብሔር እስከ ዛሬ ድረስ የሌዊን ነገድ ለየ።
31፥25 ሙሴ የእግዚአብሔርን **ቃል ኪዳን ታቦት** የሚሸከሙትን ሌዋውያንን እንዲህ ብሎ አዘዘ

እንግዲህ ከላይ ባጭሩ እንደተመለከትነው ታቦት ከነስሙ "የቃል ኪዳን ታቦት" ነው። ማለትም ከአንድ ቃል ኪዳን ጋር የተቆራኘ ስለዚያ ቃል ኪዳን የሚመሰክሩትን የምስክር ጽላቶች የያዘ ምስክር ነው። ይህም ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በሲና ተራራ የገባው የብሉዩ ኪዳን ነው። በታቦቱ ውስጥ ባሉት በምስክሩ ጽላቶች ላይ የተጻፉት አሥርቱ ቃላት ከብሉይ ኪዳኑ የማይነጣጠሉ እንደሆኑ ሁሉ የኪዳኑም ታቦት ከብሉይ ኪዳን ጋር የተቆራኘና የማይነጣጠል ነው። የሚመሰክረው ስለ ብሉይ ኪዳኑ ነውና።

ታቦት እንግዲህ ከግራር እንጨት የተሠራ በመቅደሱም በውስጠኛው ክፍል ማለትም በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የሚቀመጥ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የገባው የቀድሞው ወይም የብሉይ ኪዳን ምስክር የሆኑትን የድንጋይ ጽላቶች የያዘ የብሉዩ ኪዳን ምስክር ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታቦት ሲጠቀስ እንግዲህ ያን በሲናና ተራራ የተፈጸመውን ቃል ኪዳን የሚያመለክት ነው። ይህም የቃል ኪዳኑ ተጋቢዎች የሆኑትን እግዚአብሔርንና የእስራኤል ሕዝብን እንዲሁም የቃል ኪዳኑ የውል ስምምነት የሆነውን ሕጉን የሚያስታውስ ነው።

## 2 የብሉይና የአዲስ ኪዳን ልዩነት

ስለ ብሉይና ስለ አዲስ ኪዳን ንጽጽር ስናስብ ከሁሉ አስቀድሞ በመጀመሪያ አንድ ጥያቄ መመለስ ይገባናል። ይህም ከብሉዩ የተለየ አዲስ ሌላ ኪዳን ወይም አዲስ ውል ለምን አስፈለገ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይኖርብናል። እግዚአብሔር ገና በብሉይ ኪዳን ዘመን ነው አዲስ ኪዳን እንደሚያስፈልግ በነብያቱ የተናገረው።

ትንቢተ ኤርምያስ 31
31 እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር **አዲስ ቃል ኪዳን** የምገባበት ወራት ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር 32 ከግብጽ
አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም **እነርሱ በኪዳኔ**
**አልጸኑምና፥** እኔም ቸል አልኋቸው፥ ይላል እግዚአብሔር፡- 33 ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን
ይህ ነውና፥ ይላል እግዚአብሔር **ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ** እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም
ሕዝብ ይሆኑኛል።

በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ራሱ ስለ አዲስ ኪዳን አስፈላጊነት በትንቢት በነቢዩ ኤርምያስ አማካኝነት ይናገራል። አዲስ ኪዳን ያስፈለገበትም ዋና ምክንያት የቀድሞውን ኪዳን እግዚአብሔር ስላልጠበቀ ወይም የቀድሞው ኪዳን መሠረት የሆነው ሕጉ መጥፎ ስለሆነ አይደለም። ነገር ግን ይህ ክፍል "**እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና**" እንደሚለው ዋናው ችግር ያለው ከቃል ኪዳን ተጋቢዎቹ አንዱ ወገን ማለትም የእስራኤል ሕዝብ የቃል ኪዳኑን ውል ማለትም ሕጉን ስላልጠበቁና መጠበቅም ስላልቻሉ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ በሮሜ መልዕክቱ ሲያስረዳ እንዲህ ይላል።

ወደ ሮሜ ሰዎች 3
20 ይህም **የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤** ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና። 21 አሁን
ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ **ያለ ሕግ ተገልጦአል፥** 22 እርሱም፥ **ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ**
**ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤** ልዩነት የለምና፤ 23 ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም
ክብር ጎድሎአቸዋል፤ 24 **በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።**

ትልቁ የብሉይ ኪዳን ችግር እንግዲህ ሰው ሕግን ሁሉ ያለምንም ስህተት ማድረግና መፈጸም ባለመቻሉ ነው። ስለዚህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ሊጸድቅ ስለማይችል በሕግ ላይ ያልተመሠረተ አዲስ ቃል ኪዳን አስፈለገ ማለት ነው። የአዲሱ ኪዳን መሠረት ለሰዎች ሁሉ ኃጢያት ስርየት በሞተው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን "ያለ ሕግ" የሚገኝ ጽድቅ ነው። ይሄም ጽድቅ ሰዎች በራሳቸው ጥረት ሕግን በመጠበቅ የሚያገኙት የሰው ጽድቅ ሳይሆን "እንዲያው በጸጋው" ከእግዚአብሔር የሚቀበሉት "የእግዚአብሔር ጽድቅ" ነው።

የብሉዩ ኪዳን ትልቁ ድክመት እንግዲህ ሰዎች ናቸው። በዚህም የተነሳ ብሉይ ኪዳን ሰዎችን የሚያጸድቅ ኪዳን መሆኑ ቀርቶ ሰዎች ሕግን መጠበቅ ባለመቻላቸው ምን ያህል ኃጢያተኞች እንደሆኑ ራሳቸውን የሚያዩበትና የሚኮንኑበት (condemn) ኪዳን ሆነ። የብሉዩ ኪዳን ለሰዎች ሕግንና በድንጋይ ጽላት ላይ የተጻፉ ትዕዛዛትን ቢሰጥም ሰዎቹ ያንን ሕግ የሚጠብቁበት ኃይል ግን አልሰጣቸውም ነበር። ለዚህ ነው ገና በብሉይ ኪዳን ዘመን ከላይ ባየነው የኤርምያስ ትንቢት እግዚአብሔር በአዲሱ ኪዳን ሕጉን በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይሆን በሰዎች ልብ ላይ ራሱ እንደሚጽፍ የሚናገረው።

„... ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ...“ ኤርምያስ 31፤33

በ 2 ኛ ቆሮንቶስ መልዕክት ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የብሉይ ኪዳንን እና የአዲስ ኪዳንን አገልግሎት ሲያነጻጽር የብሉዩን "የኩነኔ አገልግሎት" ወይም "የሞት አገልግሎት" በማለት ሰዎች ኃጢያተኞች መሆናቸውን ከማሳየት በስተቀር ሊያጸድቃቸው የማይችል አገልግሎት መሆኑን ሲገልጽ በአንጻሩ ደግሞ ሰዎችን ሊያጸድቅ የሚችል በመሆኑ የአዲስ ኪዳንን አገልግሎት "የጽድቅ አገልግሎት" እያለ ይጠራዋል። በብሉዩ ኪዳን የእስራኤል ሕዝብ ሊፈጽመው የማይችሉትን በድንጋይ ላይ የተጻፈ ሕግን ተቀብለው እንፈጽማለንም ብለው ቃል ኪዳን አደረጉ ነገር ግን መፈጸም አልተቻላቸውም። አዲስ ኪዳን ግን እግዚአብሔር ራሱ ሕጉን በሰዎች ልብ ላይ የሚጽፍበት የተለየ ኪዳን ነው።

2 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 3
3 **እናንተም በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፥ *ሥጋ* በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ፥**
በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደ ሆናችሁ የተገለጠ ነው። 4 በክርስቶስም በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ
እምነት አለን። 5 ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን
አይደለንም፤ 6 እርሱም ደግሞ **በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል
ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።** 7 ዳሩ ግን የእስራኤል ልጆች ስለዚያ ስለ ተሻረው ስለ ፊቱ ክብር የሙሴን ፊት
ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ፥ **ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት** በክብር ከሆነ፥ 8
**የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም**? 9 **የኵነኔ አገልግሎት ክብር ከሆነ፥ ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት በክብር
አብዝቶ ይበልጣልና።** 10 ያ የከበረ እንኳ እጅግ በሚበልጠው ክብር ምክንያት በዚህ ነገር ክብሩን አጥቶአልና። 11 **ያ ይሻር
የነበረው በክብር ከሆነ፥ ጸንቶ የሚኖረውማ እጅግ ይልቅ በክብር ሆኖአልና።**

የአዲስ ኪዳን የኪዳኑ ውልና መሠረት ከብሉይ ኪዳን የተለየ ነው። የብሉይ ኪዳን ውል፤ እግዚአብሔር በሚሰጣቸው ምድር የእስራኤል ልጆች በሕጉ ያሉትን ትዕዛዛት ሁሉ ሊፈጽሙ፤ እግዚአብሔርም አምላክ ሊሆናቸና ሊባርካቸው፤ ባይፈጽሙ ግን እርግማን እንደሚመጣባቸው ከሰጣቸውም ምድር እንደሚያባርራቸው የሚገልጽ ውል ነው። የአዲስ ኪዳን ውል ደግሞ ከዚህ እጅግ የተለየ ነው። የውሉም መሠረት ሕጉ ሳይሆን ለዓለም ኃጢአት ሁሉ ደሙን ያፈሰሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰዎች በክርስቶስ ቢያምኑ እግዚአብሔር ኃጢያታቸውን ይቅር እንደሚላቸውና እንደሚያጸድቃቸው የሚገልጽ "ያለ ሕግ" የሆነ ውል ነው።

ወደ ሮሜ ሰዎች 3
21 አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ **<u>ያለ ሕግ</u> ተገልጦአል**፥ 22 እርሱም፥ **ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥
በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው**፤ ልዩነት የለምና፤ 23 ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና
የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ 24 **በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።**

የዮሐንስ ወንጌል 3
16 በእርሱ **የሚያምን ሁሉ** የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ
**<u>ዓለሙን</u> እንዲሁ ወዶአልና።**

ወደ ሮሜ ሰዎች 7
4 እንዲሁ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ *ሥጋ* **ለሕግ ተገድላችኋል**፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ፥ እናንተ
ለሌላው፥ **ከሙታን ለተነሣው፥ ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ።** 5 በ*ሥጋ* ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ
በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና፤ 6 አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን፥ **ከሕግ ተፈትተናል፥ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ
እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።**

አዲስ ኪዳን እንግዲህ ሰው በራሱ *ሥራ* እንደማይጸድቅና አዳኝ እንደሚያስፈልገው ተረድቶ በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋትነትና አዳኝነት አምኖ የሚድንበትና የሚጸድቅበት ዓለምን ሁሉ ሊያድን የሚችል ኪዳን ነው።

እዚህ ጋር ግን አንድ ልብ ማለት ያለብን ሁለቱን ኪዳኖች ጎን ለጎን በማካሄድ አንድም የሕግን *ሥራ* በመ*ሥራ*ት በራስ ለመጽደቅ መሞከር በሌላ ጎን ደግሞ በክርስቶስ *ሥራ* በጸጋ ለመጽደቅ መሞከር እንደማይቻል መገንዘብ ይገባናል። በአንድ በኩል በድንጋይ ጽላት ላይ ተጽፎ የተሰጠውን የሕግን *ሥራ* ሠርቶ ለመጽደቅ መሞከር፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንዲያው በጸጋ በክርስቶስ እምነት የሚገኘውን ጽድቅ ማግኘት አይቻልም። በገላትያ የነበሩ የክርስቶስ አማኞች በአንድ በኩል የሕግን *ሥራ* በመ*ሥራ*ት በሌላ በኩል ደግሞ በክርስቶስ በኩል በጸጋ ለመጽደቅ እንዳይጥሩ ትልቅ ማስጠንቂያ ተሰጥቶአቸው ነበር።

ወደ ገላትያ ሰዎች 5
2 እነሆ፥ እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ። ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም። 3 **ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት** ብዬ

ለሚገረዙት ሁሉ ለእያንዳንዶች ደግሜ እመሰክራለሁ። 4 **በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው**
**ወድቃችኋል።** 5 እኛ በመንፈስ ከእምነት የጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለንና። 6 በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት
እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና።

ወደ ገላትያ ሰዎች 3
23 እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር። 24 እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ
ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤ 25 እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች
አይደለንም። 26 በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤

የአዲስ ኪዳን ተከታዮች ከብሉይ ኪዳን ሕግ ነጻ ናቸው ማለት ግን ሕገወጥ ይሆናሉ የፈለጉትን ኃጢያት ይለማመዳሉ ማለት ግን አይደለም። በድንጋይ ላይ ከተጻፈ ከፊደል ሕግ ወጥተው ወደ መንፈስ ሕግ ይሸጋገራሉ ማለት ነው። ይህም በመንፈስ ቅዱስ እርዳታና ምሪት ከኃጢአት እየራቁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በደስታ እያደረጉ መኖርን ያጠቃልላል። የአዲሱ ኪዳን የመንፈስ ሕግ ወይም በመንፈስ የመመላለስ ሕይወት ራሱን የቻለ ሰፊ ትምህርት ስለሆነ በዚህ ክፍል አንመለከተውም (በሮሜ 8 እና በገላትያ 5 ላይ ማጥናት ይቻላል)። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን፤ ከብሉይ ኪዳን ሕግ መፈታት ማለት ሕገ ወጥ መሆን ወይም እንደፈለጉ ኃጢአትን ማድረግ እንዳልሆነ በዚህ ቦታ መጥቀስ ይገባል።

በመጨረሻም ሁለቱ ኪዳኖች እስራኤላዊ ካልሆኑ ሕዝቦች ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች እንመልከት። ቃሉ እንደሚለው ሁለቱም ኪዳኖች የመጡት ለእስራኤል ነው። ሆኖም ቀደም ብለን እንዳየነው በብሉይ ኪዳን አንዳንድ ተሰድደው በእስራኤል ከሚኖሩ ምጻተኞች (ስደተኞች) በስተቀር ሌሎች ሕዝቦች የዚህ ኪዳን ተካፋዮች አልነበሩም። የኪዳኑ ውል የሆነው የሕጉ በረከቱም ሆነ መርገሙ ከአንድ ሕዝብ ማለት ከእስራኤልና ለእነርሱ ከተሰጣቸው ምድር ጋር የተቆራኘ ነው። እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ የሰጠውና ሌሎች ሕዝቦችን (አሕዛብን) የማያካትት (exclusive)፤ በሥጋ ከእስራኤል ዘር በመወለድ ብቻ የሚገባበት ኪዳን ነው።

አዲሱ ኪዳን ግን በትውልድ እስራኤላዊ ያልሆኑትን ሕዝቦች ሁሉ የሚያካትት (inclusive) ለዓለም ሁሉ መድኃኒትና መዳኛ መንገድ እንዲሆን የተሰጠና አህዛብንም አይሁድንም በክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ እንደ አንድ ሕዝብ አድርጎ ያዋሃደ ኪዳን ነው።

የዮሐንስ ወንጌል 3
16 በእርሱ **የሚያምን ሁሉ** የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ
**ዓለሙን** እንዲሁ ወዶአልና።

ወደ ገላትያ ሰዎች 3
23 እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር። 24 እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ
ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤ 25 እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች
አይደለንም። 26 **በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤** 27 ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ
ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። 28 **አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥**
**ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።** 29 **እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም**
**ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።**

ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2
11 ስለዚህ **እናንተ አስቀድሞ በሥጋ አሕዛብ የነበራችሁ**፥ በሥጋ በእጅ የተገረዙ በተባሉት ያልተገረዙ የተባላችሁ፥ ይህን አስቡ፤ 12
በዚያ ዘመን **ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ**
ከእግዚአብሔርም ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ። 13 አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ
ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል። 14-15 እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ
በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም
ያደርግ ዘንድ፥ 16 ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው። 17
መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን፥ ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምስራች ብሎ ሰበከ፤ 18 በእርሱ ሥራ ሁላችን
በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና። 19 እንግዲያስ **ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች**
**ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።**

የአዲስ ኪዳን መሠረትና የውል ስምምነት ከብሉዩ ኪዳን ጨርሶ የተለየ ነው። የአዲሱ ኪዳን የውል ስምምነት የተመሠረተው በድንጋይ ላይ የቀረጹትን ሕግጋት በመጠበቅ ወይም ባለመጠበቅ አይደለም። ነገር ግን በክርስቶስ ብቸኛ አዳኝነት በማመን ወይም ባለማመን ላይ ነው። እንደ ብሉይ ኪዳንም የእስራኤልን ሕዝብ ብቻ አቅፎ አሕዛብን የሚያገልል አይደለም፤ ነገር ግን ለእስራኤላውያንም ለአሕዛብም፤ ለዓለም ሕዝብ ሁሉ መዳኛ እንዲሆን እግዚአብሔር የሰጠው ኪዳን ነው። በረከቱም በከነዓን ምድር ገብቶ ምድራዊ በረከትን መቀበል አይደለም፤ ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ዋናው በረከት መንፈሳዊ ነው ይህም በእግዚአብሔር ፊት መጽደቅን፣ ከፍርድ መዳንን፣ የዘላለም ሕይወት ማግኘትን፣ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንን ወዘተ የመሳሰሉትን መንፈሳዊ በረከቶችን ያካተተ ነው።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1
3 በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ **በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ** የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።

የዮሐንስ ወንጌል 1
12 ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ **የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው**፤ 13 እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።

የዮሐንስ ወንጌል 3
16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ **የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ** እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

የአዲስ ኪዳን መሠረትና የውል ስምምነት ከብሉዩ ኪዳን ጨርሶ የተለየ ስለሆነና ታቦቱ ደግሞ የብሉይ ኪዳኑ ውል የሆነውን የሕጉን የምስክር ጽላቶች የያዘ፤ ስለ ብሉይ ኪዳኑ የሚመሠከር፤ ከብሉይ ኪዳኑ ጋር የተቆራኘ ስለሆነ፤ ለአዲስ ኪዳን ምስክር ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር ያሰበውም የታቦት አገልግሎት እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በሲና ተራራ ስላደረው ቃል ኪዳን መመሥከር እንጂ በክርስቶስ ደም ስለሆነው ስለ አዲሱ ኪዳን እንዲመሠክር አይደለም።

አዲስ ኪዳን በድንጋይ ጽላት ሳይሆን በልብ ጽላት ላይ የሚጻፍ፣ ሰዎችን መኮነን ሳይሆን ማጽደቅ የሚችል ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝቡ ሁሉ የሆነ፣ በኮርማዎችና በከብቶች ደም ሳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተመሠረተ የተሻለ ኪዳን ነው።

የማርቆስ ወንጌል 14
22 ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ሰጣቸውና። እንካችሁ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። 23 ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው፥ ሁሉም ከእርሱ ጠጡ። 24 እርሱም፦ ይህ **ስለ ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን** ደሜ ነው።

## 3 ታቦት በዮሐንስ ራእይ

እንግዲህ በሁለቱ ኪዳኖች መካከል ያሉት መሠረታዊ ልዩነቶች ግልጽ ከሆኑልን፤ በመጀመሪያ ወደ ተነሳንበት የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ እንመለሳለን።

የዮሐንስ ራእይ
11፥19 በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ።

ይህ ክፍል በአንዳንዶች ላይ ጥያቄና ግራ መጋባት ሲፈጥር ይታያል። በአዲስ ኪዳን የታቦት አገልግሎት ሳይጠቀስ ቆይቶ ድንገት በራእይ መጽሐፍ ላይ የብሉይ ኪዳኑ ታቦት ሲጠቀስ ትንሽ ግር የሚላቸው ሰዎች አሉ።

በዚህ ክፍል የብሉይ ኪዳኑ ታቦት መጠቀሱ ለምንድነው? ክፍሉስ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድነው? የክርስቶስ ተከታዮች እንደ ብሉይ ኪዳን አይነት ታቦት ሠርተው የብሉዩን ሥርዓት እንዲያካሂዱ ነው የሚያስተምረው ይህ ክፍል? አይደለም። የክርስቶስ ተከታዮች ወደ ብሉዩ ኪዳኑ ሥርዓት ይመለሱ ወይም የብሉዩንና የአዲሱን ሥርዓት ጎን ለጎን ያካሂዱ የሚል መልዕክት ነው በዚህ ክፍል ያለው? ይህን የሚያሳይ አንዳችም ነገር በዚህ ክፍል የለም። እንዲህማ ቢሆን አዲስ ኪዳንም ባላስፈለገ ነበር። ሁለቱን ኪዳኖች ጎን ለጎን በማካሄድ በሁለቱም በኩል ለመጽደቅ እንደማይቻልም ሁሉ ተመልክተናል፤ ስለዚህ ይህ ክፍል አዲስ ኪዳን ደጋግሞ ያስተማረውን ትምህርት የሚቃረን ወይም የሚገለብጥ ትምህርት ጨርሶ የለውም።

ታዲያ በዚህ ክፍል የታቦቱ መታየት ለምን አስፈለገ? ሊስተላለፍስ የተፈለገው መልዕክት ምንድነው? የዚህን ክፍል መልእክት ከመመልከታችን በፊት ስለ ዮሐንስ ራእይ አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮችን እንመልከት።

አንደኛ የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ የትንቢት መጽሐፍ ነው።

የዮሐንስ ራእይ 1
1 ***ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን*** ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥ 2 እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መሰከረ። 3 ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ **የትንቢቱን ቃል** የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።

ይህም ማለት እንደ ብሉይ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍት ሁሉ ይህም የዮሐንስ ራእይ በአብዛኛው ወደፊት ሊመጣ ስላለውም ነገር የሚተነብይ መጽሐፍ ነው።

የዮሐንስ ራእይ 1
19 እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን **ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን** ጻፍ።

የዮሐንስ ራእይ እንግዲህ አሁን ስላለው ወይም ዮሐንስ በጻፈበት ጊዜ ስለነበረው ብቻ ሳይሆን ወደፊት ስለሚሆነውም የሚተነብይ መጽሐፍ ነው። እንዲያውም ከምዕራፍ 4 ጀምሮ ያለው ክፍል ወደፊት ሰለሚሆነው የሚተነብይ ስለወደፊት የሚናገር ትንቢት እንደሆነ በግልጽ ተጠቅሶአል።

> የዮሐንስ ራእይ 4
> 1 ከዚያ በኋላም አየሁ፥ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ። ወደዚህ
> ውጣና **ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ** አለ።

ስለዚህ መነሻ የሆነን በምዕራፍ 11 የሚገኘው ጥቅስ የሚናገረው ወደፊት ስለሚሆን ትንቢት እንደሆነ በመጀመሪያ መረዳት ይገባናል።

ሌላው የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ብዙ ምሳሌያዊ ምልክቶችን (symbols) ያካተተ መጽሐፍ መሆኑን ማወቅ መጽሐፉን በሚገባ ለመረዳት ይጠቅመናል። ነገር ግን ምሳሌያዊ ምልክቶቹን ራሳችን እንደፈለግንና እንደመሰለን የምንተረጉመው ሳይሆን የምልክቶቹ ተርጓሚ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ መረዳት አለብን።

የዮሐንስ ራእይ የትንቢት መጽሐፍ እንደመሆኑ መጽሐፉን በይበልጥ ለመረዳት በመጽሐፍ ቅዱስ ስለተነገሩ ትንቢቶች መሠረታዊ መረዳት ሊኖረን ይገባል። በዚህ ጽሑፍ የተነሳንበትን ክፍል ለመረዳት የሚያስችለንን መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን ብቻ በአጭሩ እንመለከታለን።

የዮሐንስ ራእይ የሚናገራቸው የወደፊት ትንቢቶች በአብዛኛዎቹ በብሉይ ኪዳን ዘመን በነበሩ ነብያትም የተተነበዩ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ዮሐንስ ራእይ ከምዕራፍ 6 እስከ ምዕራፍ 19 ያለው ክፍል በዳንኤል መጽሐፍ ምዕራፍ 9 ላይ ስለተነገረው ሰባኛው ሱባዔ ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ከመምጣቱ በፊት ስለሚሆነው ስለ መጨረሻው የሰባት ዓመት ታላቁ የመከራ ዘመን የሚናገር ነው። በተለይ ደግሞ ከሰባት ዓመቱ አጋማሽ ጀምሮ ማለትም በተቀሪዎቹ ሶስት ዓመት ተኩል ጊዜያት እጅግ ታላቅ መከራ በምድር ላይ እንደሚሆን ጌታም ታናግሮአል።

> የማቴዎስ ወንጌል 24
> 21 በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና።
> 22 እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ።

በመከራው ዘመን ይሆናሉ ተብለው በብሉይም በአዲስም ከተተነበዩት ትንቢቶች አንዱ የእስራኤል ሕዝብ ሙሉ በሙሉ ወደ አዲሱ ኪዳን መግባትን የሚናገር ትንቢት ነው።

> ትንቢተ ሕዝቅኤል 20
> 33 እኔ ሕያው ነኝና በበረታች እጅና በተዘረጋች ክንድ በፈሰሰችም መዓት እነግሥባችኋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 34
> ከአሕዛብም ዘንድ አወጣችኋለሁ ከተበተናችሁባትም አገር ሁሉ በበረታች እጅና በተዘረጋች ክንድ በፈሰሰችም መዓት
> እሰበስባችኋለሁ። 35 ***ወደ አሕዛብም ምድረ በዳ አመጣችኋለሁ በዚያም ፊት ለፊት ከእናንተ ጋር እፋረዳለሁ።*** 36 **በግብጽ**
> **ምድረ በዳ ከአባቶቻችሁ ጋር እንደ ተፋረድሁ እንዲሁ ከእናንተ ጋር እፋረዳለሁ**፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ 37 ከበትርም
> በታች አሳልፋችኋለሁ ***ወደ ቃል ኪዳንም እስራት አገባችኋለሁ*** 38 ከእናንተም ዘንድ ዓመፀኞችንና የበደሉኝን እለያለሁ
> ከኖሩባትም ምድር አወጣቸዋለሁ፥ ወደ እስራኤል ምድር ግን አይገቡም እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።

በዚህ ክፍል ልክ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ምድር አውጥቶ በምድረበዳ ፊት ለፊት ከእነርሱ ጋር እንደ ተፋረደና ወደ ብሉዩ ቃል ኪዳን እንዳስገባቸው እንዲሁ እንደገና እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በምድረበዳ ፊት ለፊት እንደሚፋረድና ወደ አዲሱ ኪዳን እንደሚያስገባቸው የተነገረ ትንቢት ነው። "ወደ ቃል ኪዳንም እስራት አገባችኋለሁ" ቁጥር 37። እግዚአብሔር እንግዲህ እስራኤልን ወደ አዲሱ ኪዳን የሚያስገባቸው ልክ ወደ ብሉዩ ኪዳን እንዳስገባቸው አይነት በምድረበዳ ከሕዝቡ ጋር ፊት ለፊት በመፋረድ ነው። በሮሜ 11 ላይም የእስራኤል ሕዝብ የተላከላቸውን መሲሕ አሁን መቀበል እንዳልቻሉና በመንፈሳዊ እንቅልፍ ውስጥ እንዳሉ ነገር ግን ወደፊት ሕዝቡ ክርስቶስን እንደ መሲሕአቸው እንደሚቀበሉና እንደሚድኑ በሰፋት ተብራርቶአል።

እንግዲህ በራእይ መጽሐፍ ወዳለው ወደ ተነሳንበት ጥቅስ ስንመለስ ይህንን የተነሳንበትን ጥቅስ በሚገባ ለመረዳት ጥቅሱ የሚገኝበትን ምዕራፍ 11 እና ምዕራፍ 12 ን በሙሉ መመርመር ይገባል። በተለይ ከምዕራፍ 11፤15 ጀምሮ ማለትም ሰባተኛው መልአክ መለከት ከነፋ በኋላ እስከ ምዕራፍ 12 መጨረሻ ያለው የተያያዘ ሃሳብ ነው። በዚህም ክፍል ከታቦቱ ጋር ተያይዛ በቀጣዩ በምዕራፍ 12 የተጠቀሰች አንዲት ሴት አለች። ወደ ታቦቱ ከመምጣታችን በፊት ከታቦቱ ጋር ተያይዛ በተከታታይ ስለተጠቀሰችው ስለዚች ሴት በመጀመሪያ እንመልከት።

ይህች ሴት በምዕራፍ 11 የመጨረሻ ጥቅስ ከሆነው ከታቦቱ ጥቅስ ጋር አብራ ተያይዛ ከምዕራፍ 12 ቁጥር 1 ጀምሮ የተጠቀሰች ናት። እርሷም ከታቦቱ ጥቅስ ጋር ወዲያው ተከትላ የተገለጸች ሴት ስለሆነች የእርሷን ማንነት መረዳት ታቦቱ ለምን እዚህ ክፍል ላይ እንደተጠቀሰ እንድንረዳ ያግዘናል።

> (የዮሐንስ ራእይ 11) 19 በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም

ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ። (የዮሐንስ ራእይ 12) 1 ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ
ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች። 2 እርስዋም ፀንሳ
ነበር፥ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጭንቃ ጮኸች። 3 ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና
አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥ 4 ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሢሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው።
ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ። 5 አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው
ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ። 6 ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ
ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች። 7 በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤
ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፥ አልቻላቸውምም፥ 8 ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ
አልተገኘላቸውም። 9 ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ
ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።

በዚህ ክፍል ቁጥር 1 ላይ ስለ ሴቲቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር "**ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ**" ብሎ ይጀምርና የታየው ምልክት ምን እንደሆነ ሲገልጽ "**ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች**" ይላል። ስለዚህ ይህች ሴት ስለ አንድ ነገር የምታመለክት ምልክት (symbol) ናት ማለት ነው። መጽሐፍ ቁዱስ ራሱ ምልክት እንደሆነች ይናገራልና።

ሴቲቱ ወይም ሴትዮዋ ምንን እንደምታመለክት ወይም ትርጉሟ ምን እንደሆነ ለመረዳት የተገለጸችበትን ዓረፍተ ነገር እንመልከት። ሴቲቱ ፀሐይ እንደተጎናጸፈች፤ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች እንዳላትና በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የነበራት ሴት እንደሆነች መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። ይህች ሴት እንግዲህ በፀሐይ በጨረቃና በአሥራ ሁለት ክዋክብት የምትመሰል ሴት ናት። ይህ ሴቲቱ የተገለጸችበት አገላለጽ ዘፍጥረት ላይ ዮሴፍ ካለመው ሕልም ጋር ተመሳሳይ ነው።

ኦሪት ዘፍጥረት
9 ደግሞም ሌላ ሕልምን አለመ፥ ለወንድሞቹም ነገራቸው፥እንዲህም አለ፦ እነሆ ደግሞ ሌላ ሕልምን አለምሁ እነሆ **ፀሐይና
ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋክብትም** ሲሰግዱልኝ አየሁ። 10 ለአባቱና ለወንድሞቹም ነገራቸው አባቱም ገሥጸው፥ እንዲህም አለው፦
ይህ ያለምኸው ሕልም ምንድር ነው? **በውኑ እኔና እናትህ ወንድሞችህም** መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆን?

ይህ ክፍል ግልጽ እንደሚያደርገው ፀሐይና ጨረቃ አሥራ ሁለቱም ክዋክብት ሁሉ የእስራኤል ሕዝብ ምልክቶች ናቸው። አሥራ ሁለቱ ክዋክብት የእስራኤልን ሕዝብ አሥራ ሁለት ነገዶች ፀሐይና ጨረቃ ደግሞ የነገዶቹን አባትና እናት የሚያመለክቱ እንደሆነ በግልጽ ተቀምጦአል። ያዕቆብ የእስራኤል ሕዝብ አባት እንደሆነና "እስራኤል" የሚለው ስም ራሱ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ያወጣለት ስም እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘፍጥረት 32፤27-28)። የአሥራ ሁለቱም የእስራኤል ሕዝብ ነገዶች አባቶች ዮሴፍን ጨምሮ አሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ እንደሚተረጉመው ይህቺ ሴት እንግዲህ የእስራኤልን ሕዝብ የምታመለክት ናት።

ሌላው ስለዚህች ሴት በቁጥር 5 የተጠቀሰው ነገር አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ወንድ ልጅ እንደ ወለደች እና ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ እንደተነጠቀ ነው። አሕዛብን በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውና ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የተነጠቀው ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ አያጠያይቅም። ክርስቶስም ከእስራኤል ሕዝብ ስለተወለደ ይህን ወንድ ልጅ የወለደችው ሴት የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚያመለክት ሁለተኛው ማረጋገጫ ነው።

ወደ ሮሜ ሰዎች 9
4 **እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና**፥ ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም ሥርዓት የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ
ናቸውና፤ 5 አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ **ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ**፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ
አምላክ ነው፤ አሜን።

ሌላው ከሴትዮዋ ጋር አብሮ በራእይ 12፤7 ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር መልአክ ሚካኤል ስለ ሴትዮዋ ማንነት ሌላ ፍንጭ የሚሰጠን ነው። ምክንያቱም ሚካኤል የእስራኤል ሕዝብ መልአክ እንደሆነ በትንቢተ ዳንኤል ተጽፎአልና።

ትንቢተ ዳንኤል 12
1 በዚያም ዘመን **ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል** ይነሣል ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ
እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል።

እንግዲህ ከላይ ካየናቸው መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ መሠረት ካደረጉ ትርጉሞች እንደምንረዳው ከታቦቱ በመቀጠል ወዲያው የተጠቀሰችው ሴት የምታመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ከላይ በሕዝቅኤል 20 ላይ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ወደ በረሃ አውጥቶ በዚያ እንደተፋረዳቸውና ወደ ብሉዩ ኪዳን እንዳስገባቸው እንዲሁ እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ከተበተኑበት አገሮች ከተሰበሰቡ በኋላ በምድረበዳ ፊት ለፊት እንደሚፋረዳቸውና ወደ አዲሱ ኪዳን እሥራት ውስጥ እንደሚያስገባቸው ተመልክተናል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ እንዳወጣቸውና ከፈርዖን እንዳዳናቸው ሲናገር በዘጸአት ላይ እንዲህ ብሎ ነው የሚገልጸው።

ኦሪት ዘጸአት
19፥4 በግብፃውያን ያደረግሁትን፥ **በንስርም ክንፍ** እንደተሸከምኋችሁ፥ ወደ እኔም እንዳመጣኋችሁ አይታችኋል።

በዚህም በራእይ ምዕራፍ 12 ላይ ተመሳሳይ ነገር ነው የምንመለከተው።

የዮሐንስ ራእይ 12
6 ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።
14 ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን፥ ዘመናትም፥ የዘመንም እኵሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሀ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ **ንሥር ክንፎች** ተሰጣት።

ሴቲቱ ከዘንዶው ማለትም በቁጥር 9 ላይ ማንነቱ እንደተገለጸው ከሰይጣን እንድታመልጥና "በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ" እንድትሸሸ "ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች" እንደተሰጣት እናነባለን። ይህም ልክ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ምድር ከፈርዖን እጅ እንዳስጣላቸው እንዲሁ በታላቁ መከራ ዘመን እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ዘንዶው ከሚያስነሳባቸው ስደት እንደሚያስመልጣቸው የሚያመለክት ነው።

የሴቲቱ ሽሽትም ከሰባቱ ዓመት የመከራ ዘመን የመጨረሻውን ኣጋማሽ ማለትም ለሶስት ዓመት ተኩል እንደሆነም ተገልጾአል። ቁጥር 6 ላይ "ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን" ብሎ ሲጠራው ቁጥር 14 ላይ ደግሞ "ዘመን፥ ዘመናትም፥ የዘመንም እኵሌታ" ይለዋል። ማለትም አንድ አመት፥ ሁለት ዓመትና ግማሽ አመት ማለት ነው።

እንግዲህ በዚህ በሽሽት ዘመንና በበረሃ ነው እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳኑ ሁሉ ፊት ለፊት ተገልጦ ከተፋረደ በኋላ ወደ አዲሱ ኪዳን የሚያስገባቸው።

ምዕራፍ 12 ከመጀመሩ በፊት የታቦቱ መታየት እንግዲህ አሁን ይበልጥ ግልጽ ይሆንልናል። አንደኛ ቀድመን እንዳጠናነው ታቦት በእግዚአብሔርና በእስራኤል ሕዝብ መካከል የተደረገው የብሉዩ ቃል ኪዳን ምስክር ነው። ይህ የቀድሞው ኪዳን ደግሞ ሌሎችን ሕዝቦች ሳይሆን እስራኤልን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ እንደሆነ ተመልክተናል። ይሄንንም የብሉዩን ኪዳን እስራኤል ባለመጠበቃቸውም ምክንያት አዲስ ኪዳን እንዳስፈለገም አይተናል። ስለዚህ በዮሐንስ ራእይ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝቡን ከመፋረዱ በፊት ማለትም ከምዕራፍ 12 በፊት እና በምዕራፍ 11 መጨረሻ የታቦቱ መታየት እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የሚፋረድበትና ወደ አዲሱ ኪዳን የሚያስገባበት ጊዜ መድረሱን የሚያመለክት ነው። ምዕራፍ 12 ደግሞ የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን የብሉዩን ኪዳን እንዳልጠበቁ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በበረሃ ተፋርዶ በሕዝቅኤል እንደተተነበየው ወደ አዲሱ ኪዳን የሚይስገባበትን ቅድመ ሁኔታ የሚያሳይ ነው።

ቀደም ብለን እንዳየነው በመጽሐፍ ቅዱስ ታቦት ሲጠቀስ ያን በሲናና ተራራ የተፈጸመውን ቃል ኪዳን የሚያመለክት ነው። ይህም የቃል ኪዳኑ ተጋቢዎች የሆኑትን እግዚአብሔርንና የእስራኤል ሕዝብን እንዲሁም የቃል ኪዳኑ የውል ስምምነት የሆነውን ሕጉን እንደሚያስታውስ አይተናል።

በዚህ በራእይ ላይም ታቦት ያንን በሲና ተራራ የተደረገውን የብሉዩን ኪዳንና የስምምነቱ አካል የሆኑትን እግዚአብሔርን፣ የእስራኤልን ሕዝብና ሕጉን የሚያመለክት ነው። እንዲያውም ከታቦቱ ጋር አብረው በዚህ በራእይ የተጠቀሱት "መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ" ወዘተም እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የብሉዩን ቃል ኪዳን ሲገባ በሲና ተራራ የሆነውን ሁኔታ የሚያስታውሱ ናቸው።

የዮሐንስ ራእይ
11፥19 በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ **መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ** ታላቅም በረዶ ሆነ።

ኦሪት ዘጸአት 19
16 እንዲህም ሆነ በሦስተኛው ቀን በማለዳ ጊዜ **ነጐድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና እጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምጽ** በተራራው ላይ ሆነ በሰፈሩም የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ተንቀጠቀጡ። 17 ሙሴም ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘት ከሰፈር አወጣቸው ከተራራውም እግርጌ ቆሙ። 18 **እግዚአብሔርም በእሳት ስለ ወረደበት የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር** ከእርሱም እንደ እቶን ጢስ ያለ ጢስ ይወጣ ነበር፥ **ተራራውም ሁሉ እጅግ ይናወጥ ነበር**።

ስለዚህ እንደ ብሉይ ኪዳኑም ይህም ታቦት የተጠቀሰበት የራእይ ክፍል እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለውን ጉዳይ የሚያሳይ፤ የእስራኤልን የወደፊት ዕጣ የሚመለከት ነገር ነው እንጂ የክርስቶስ ተከታዮች በአዲስ ኪዳን ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን የታቦት አገልግሎት እንዲጀምሩ የሚያስተምር አይደለም።